የደቀ መዝሙርነት መርሖዎች

የክርስትና ሕይወት መርሖዎች

የመሪዎች መመርያ

# የወንጌል ስርጭት መንደርደርያ

## ትምህርት 8: የወንጌል እዉነት ምንድን ነዉ – የሃጥያት ችግሩ

## መግቢያ

ይህ ትምሕርት ከደቀመዝሙርነት መርሖዎች የትምሕርት መድብሎች አንዱ አካል ሲሆን፣ ርዕሱም “የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ” የሚል ነዉ። የዚህ ተከታታይ ትምህርት ዓላማ፣ ተሳታፊዎች ወንጌልን በብቃት ለሌሎች በማካፈል (በማሠራጨት) ዉጤታማ እንዲሆኑ፣ ማስታጠቅና ማዘጋጀት ነዉ። እግዚአብሔር ለአገልግሎት (ለሚኒስትሪ) እንዴት እንደሚያስታጥቀን መረዳት፤ የወንጌል መልእክታችንን፥ ለተለያዩ የዓለም እይታ ወይም አመለካከቶች እንዴት እንደምናዘጋጅ እናስተዉላለን። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ዉስጥ የተገኘዉንና፤ የማይለወጠዉን የተስፋ መልእክት፥ ወይም የምሥራች ቃል፤አሁንም ገና ክርስቶስን ወደ አላወቀዉ ዓለም እንድናመጣ ይረዳናል።

.

## ታሳቢ ተደራሾች

የዚህ ትምህርት ታሳቢ ተደራሾች በመሰረታዊ የክርስትና ህይወት ላይ ማነቃቂያ የሚሹ አዳዲስ ክርስትያኖች እና የክርስትና እምነትን እና አኗኗርን ለማስተማር የሚዘጋጁ ክርስትያኖች ናቸዉ። ከዚህም ባለፈ የክርስትና አስተሳሰብ የሚስባቸዉ ሰዎች ይህ ትምህርት እለታዊ ኑሮዋቸዉን በሚኖሩበት ወቅት እና ምርጫዎቻቸዉን በሚያስተካክሉ ወቅት አጋዠ ሆኖ ያገኙታል።

የመሪዎች መመሪያ አንተን እንደ መሪ የማዘጋጀት እና የማገዝ አላማ ነዉ ያለዉ። ይህ የትምህርት ምምሪያ ከሌሎች ከዚህ በተጠቀሰዉ ድህረ ገጽ(www.DEamharic.org) ላይ የሚገኙ “የደቀ መዝሙራን መርሆዎች” የትምህርት ግባቶች ጋር በጥምረት መጠቀም ይቻላል።

በተለይ ካልተገለጸ በቀር፥ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ 1954 ዓምከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድቶ የታተመ ነዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/licensing ይመልከቱ.

# የወንጌል ስርጭት መንደርደርያ

## ትምህርት 8 ፡ የወንጌል እዉነት ምንድን ነዉ – የሃጥያት ችግሩ

አላማ

የዚህ ትምህርት አላማ እግዚአብሄር ለምን ወንጌልን እንደሰጠን ማብራራት ነዉ። ወንጌል በምድር ላይ ለተንሰራፋዉ ሃጥያት የእግዚአብሄር መፍትሄ ነዉ።

የመሪዎች ማስታወሻ

ሃጥያት ከተጀመረ ግዜ ጀምሮ እግዚአብሄር ሃጥያትን የሚያሸንፍበት እና ወሎ አድሮም ሞትን ድል የሚነሳበት መንገድ አለዉ። ይህ ትምህርት ችግር ስለሆነዉ ሃጥያት እና መፍትሄ ስለሆነዉ ወንጌል ነዉ ዳሰሳ የሚያደርገዉ። የምናቀርበዉ እዉነታ አንገብጋቢነት በጊዜ ሂደት እየተረዳን እያለ በተስፋ እና በጽናት መቆም ግን አስፈላጊ ነዉ። እግዚአብሄር በህይወት ቃላት እና በይቅርታ ሞልቶናል፡ እነኝህን ቃላተ እስከአሁን ድረስ ላላመኑት ልናደርስላቸዉ ይገባል። መጽሃፍ ቅዱስ የሰይጣንን የጥፋት እና የሞት እቅድን በምን መልኩ ልናልፈዉ እንደምንችል ይገልጽልናል። ምንም እንኳዋን ማመን ቢሳናቸዉም ሰዎች ሃጥያተኞች ናቸዉ፡፡ የሃጥያት ዉጤት የሆኑትን እንደ ሞት፣ ስቃይ፣ ብቸኝነት እና ፍርሃትን በአካባቢያቸዉ ሊመለከቱ ይችላሉ። ከዚህ ሁሉ ክፉ ማምለጥ የማይሻ ማን አለ? ወንጌልን ለተሳታፊዎች ለማካፈል በአዲስ ስሜት ተነቃቃ። ሆነም ቀረ ይህ ከሁሉ የበለጠ ዜና ነዉ።

# መግቢያ

ከሚከተሉት ጥያቂዎች ዉስጥ ቡድኖችህን ለመጠየቅ ሁለት ወይንም ሶስት ጥያቄዎች ምረጥ

- በቅርቡ የተቀበልከዉ መልካም ዜና ምንድን ነዉ? ማን ነበር ያካፈለህ ምንስ ተሰማህ? ዜናዉን ምን ነበር መልካም ያደረገዉ?
- ጋዜጦችን አንብበህ ታዉካለህ? ወይንም ደግሞ ወይ በራዲዮ ወይ ደግሞ በተለቪዠን የዜና ፕሮግራም ተከታትለህ ታዉቃለህ? በአለማችን ላይ መልካሙ ዜና ነዉ ወይንስ መጥፎዉ ዜና የሚበዛዉ? መጥፎዉ ዜና መልካሙን ዜና ሸፍኖት የሚታየዉ ለምን ይመስልሃል?
- ጓደኞችህና ቤተሰቦችህ ስለራሳቸዉ ሃጥያት ምን ያህል ያውቃሉ?

# ጥናት

### አስትምር

- **ወንጌል የሚለዉ ቃል ምን ማለት ነዉ?** ወንጌል የሚለዉ ቃል ‘መልካም ዜና’ ማለት ነዉ ፡፡ ይህ ዜና ለሁሉም ሰዉ መልካም ዜና ነዉ። ሁሉም ሰዉ አንድ አይንት ችግር ነዉ ያለበት። መፍትሄዉ ደግሞ ወንጌል ነዉ።

- ወንጌል በእግዚአብሄር የተሰጠ እንጂ በሰዉ የተፈጠረ አይደለም። በመለከታዊ ሃይል የተቀኘ ወይንም የእግዚአብሄር ትንፋሽ ነዉ።(2ኛ ጢሞቲዎስ 3:16) አስፍተዉ ሲመለከቱት ወንጌል ማለት መጽሃፍ ቅዱስ በሙሉ ማለት ነዉ 9ሁሉም ቅዱሳን መጽሃፍት)።

- ወደ እዉነቱ በጥልቁ ትገቡ ዘንድ የሚከተሉትን ጥቅሶች በቡድን አንብቡዋቸዉ። እኒህ ቃላት ከእግዚአብሄር እንጂ ከሰዉ አደሉም የሚለዉን ቁልፍ ሃሳብ ተወያዩበት።

  - 1ኛ ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች 2:7-10
  - ወደ ሮሜ ሰዎች 1:1
  - ወደ ገላትያ ሰዎች 1:11-12
  - 2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:21
  - 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:13

- <u>**ወንጌል ለምን ነበር የተሰጠዉ?**</u>

  - ወንጌል የተጻፈበት አላማ ወደ እግዚአብሄር የምንመለስበትን መንገድ ለማሳየት ነዉ። እኛ የተፈጠርንበት አላማ ደግሞ ድልን ወደ እግዚአብሄር ለማምጣት ነዉ። እግዚአብሄር ከእኛ ጋር ወዳጅነትን ከመመኘቱም በላይ በእኛ ህይወት ዉስጥ ሞገስን ማግኘት ይሻል።በአምሳሉ እንደ አንድ የቤተሰቡ አባል የተፈጠርን ነን። ይህ ነዉ የተፈጠርንለት አላማ።

    - ትንቢተ ኢሳያስ 43:1-7
    - የዮሃነስ ራእይ 4:11

## ስራ

- የሚከተሉትን ጥቅሶች አስባቸዉ እና እግዚአብሄር እንደ አላማዉ የኖርን ገዜ (ከፍ ከፍ ሰናደርገዉ) የገባልንን ቃል ዘርዝራቸዉ።

  - የማቴዎስ ወንጌል 11:28-29
  - ትንቢተ ኢሳያስ 10:29-31
  - ትንቢተ ኤርሚያስ 29:11
  - መጽሃፈ ምሳሌ 1:33
  - የዮሃንስ ወንጌል 14:27
  - ወደ ሮሜ ሰዎች 10:9

## አስተምር

- **ችግሩ ምንድን ነዉ?** ይህ ከእግዚአብሄር ጋር የነበረ ወዳጅነት የተበላሸዉ ሃጥያት ወደ ምድር የመጣች ግዜ ነዉ። ሃጥያት እኛን ከእግዚአብሄር ከመለያይቱም በላይ ከእርሱ ጋር ያለንን ገንኙነት አበላሽቶታል። ይህንን ችግር ሁሉም የሰዉ ዘር ይጋራዋል። ከሃጥያት ጋር ነዉ የተወለድነዉ። ይህ ልናመልጠዉ የማንችለዉ ጉዳይ ነዉ። ፈጹም የሆነ ህይወት መኖር የማይቻለን ነን።

  - መጽሃፈ መክብብ 7:20
  - ወደ ሮሜ ሰዎች 3:10

- ***ሃጥያት ወደ አለም እንዴት እንደገባ፡*** ወንጌልን በምታካፈል ግዜ ፍጹም ልትዘለዉ የማይገባህ ቁልፍ ነጥብ ሲጀመር እንዴት ብለን ወደእዚህ ምስቅልቅል ዉስጥ ገባን የሚለዉን ነዉ። መዳን የሚለዉን የተወሳሰበ ሃሳብ ለመረዳት ሃጥያት ወደእዚህ አለም እንዴት ገባ የሚለዉን ሃሳብ ጠንቃቄ በተሞላዉ መንገድ ማብራራቱ አጋዥ ነዉ። ከዛም በላይ በሌላ አለማዊ አመለካከት ውስጥ ያሉ ሰዎች ላይ ያለዉን የተዛባ አመለካከት ለመከፈት ጥሩ መንደርደርያ ይሆናል።

  - ስለ እነዚህ ሃሳቦች ከሌሎች ጋር በምትወያይ ግዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ማጉላት ያስፈልግሃል፣

    - የአዳም ሃጥያት መንፈሳዊዉንም አካላዊዉንም ሞት አስከትሉዋል (<u>ኦሪት ዝፍጥረት 3:1-7</u> <u>ኦሪት ዘፍጥረት 3:19</u>)

- በአዳም በኩል ሃጥያት ወደ ሰው ዘር ተላለፈ (ወደ ሮሜ ሰዎች 5:12) በሎም በተወራራሽንት የሰዉ ልጅ በተፈጥሮ ሃጥያተኛ ሆነ (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:3)
- የሰዉ ዘር በሙሉ ሃጥያት መስራት ቀጠለበት (ወደ ሮሜ ሰዎች 3:23 መዝሙረ ዳዊት 14:3)
- ከሃጥያትም የተነሳ በመንፈስ ሙዉቶች ሁነናል። በእግዚአብሄር ፊትም መኖር አይቻለንም (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:1-15)
- እግዚአብሄር ፍጹም ጻድቅ እና ትክክለኛ ስለሆነ ቅጣቱን ሳያገኝ የሚያልፍ ሃጥያት የለም። (ኦሪት ዝዳግም 32:4 ወደ ሮሜ ሰዎች 1:18)
- የሃጥያት ዋጋዋ ሞት ነዉ (ወደ ሮሜ ሰዎች 6:23)

➢ የሃጥያትን ዉግዘት ከእግዚአብሄር ይቅርታ ዉጭ ልናመልጥበት የምንችልበት መንገድ የለም። ሰይጣን ያለ እረፍት እኛን ሊያታልለን ከመሞከር እና የእግዚአብሄርን ፍቃድ እንዳናሟላ ከመከላከል አርፎ አያዉቅም። ከሆኑ ሰዎች ጋር እያወራህ ከሆነ እና ሰዎቹ የሰይጣንን እቅድ ከህይወታቸዉ ማስወገድ የሚሹ ከሆነ የእግዚአብሄርን እቅድ መስማቱ በጣም ያስደስታቸዋል። እግዚአብሄር ሃጥያትን እና ሞትን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ግዜ የማሸነፍ እቅድ አለዉ።

| ሰይጣን ለእኛ ያለዉ አላማ | እግዚአብሄር ለእኛ ያለዉ አላማ |
|---|---|
| • ጸጸት<br>• ስጋት<br>• ሃጥያት<br>• ሞት<br>• ስቃይ<br>• ለሃጥያት ባርነት<br>• ከእግዚአብሄር ጋር እስከዘላለሙ መለያየት | • ሰላም እና ደስታ<br>• በፈተና ግዜ ድጋፍ<br>• ቅዱስ ህይወት<br>• የተትረፈረፈ ህይወት<br>• ለሃጥያት ይቅርታ<br>• ነጻነት በኢየሱስ<br>• ከእግዚአብሄር ጋር የዘላለም ህይወት |

# ውይይት

❖ መልካሙን ዜና ከምታስተምረበት ዘዴዎች መካከል ጥቂቶቹ እንዴት ያሉ ናቸዉ?

❖ አማኝ ያልሆኑ አንዳንድ ጓደኞችህን ሳትወነጅል ከሃጥያት ጋር ስለተያያዘዉ ችግራቸዉ ንቃተ ህሊናን እንዲያዳብሩ እንዴት ልትረዳቸዉ ትችላለህ? እንዴት ያሉ ጥያቄዎችን ልትጠይቃቸዉ ትችላለህ ? ስለራስህ ህይወት ምን ልትነግራቸዉ ትችላለህ?

❖ ሰይጣን ሃሳብህን ወይንም ዉሳኔህን ሊጫነዉ ሲሞክር ምን ታደርጋለህ? ከታዘብካቸዉ የሰይጣን አሰራር ዉስጥ ጥቂቱን ጥቀስ። እኛ እንደ ክርስቲያን ሰይጣንን መፍራት አለብን? ለምን?

# ጸሎት

ትምህርትህን ብጸሎት ዝጋ። እግዚአብሄርን ስለልጁ እና ለሃጥያታችን ይቅርታን ስለመቸሩ አመስግን። በእርግጥም ይህ መልካም ዜና ነዉ። ከሃጥያት ጋር የተያያዙ ችግሮቻችንን በራሳችን ሃይል መፍታት አይቻለንም ነበር።፡ከእርሱ ጋር ዳግም ግንኙነት ይኖረን ዘንድ መንገድ የከፈተዉን እግዚአብሄር አመስግኑ። ተሳታፊዎች ወንጌል ላይ ባላቸዉ ግንዛቤ ዉስጥ የእግዚአብሄርን ፍቅር በበለጠ ይገነዘቡ ዘንድ ጸልይ።.